

ፍትህን ፍለጋ!

# ፍትህን ፍለጋ!



(ለአበራ የማነአብ)

ርግብ ሆነህ በረህ...፣
አድማስን አቋርጠህ፣
ለሰላም፣ ለፍትህ፣ ለሕዝብ ክብር ስትል፣
በዘምባባ ቀንበጥ ጠመንጃን ልታስጥል፣
ቆርጠህ መምጣትህን በገቢር ሲረዱ፣
ጠመንጃ አምላኪዎች በፍርሃት ሲርዱ፣
ያገዱህ መስሏቸው ከቆራጥ ትግልህ መስክ፣
በፈሪ ልባቸው ተናንቋቸው እልክ፣
አወረዱህ አሉ? ከርቸሌ ወህኒ ቤት፣
የነርሱ መኖሪያ መሆን ወዳለበት!

አልተረዱም እንጅ፣
ግብርህ እንደ ስምህ ደምቆ እንደአበራ፤
አላወቁም እንጅ፣
ትግልህ ለብዙኃን መንገድ እንደመራ፤
አልገባቸውም እንጅ፣
የዓላማህ ጽናት ጀግና እንደሚያፈራ፤

ቢረዱማ ኖሮ ልብ ቢኖራቸው፣
ህሊና ቢገዙ ሃቁማ ቢያንቃቸው፣
በሕዝብ ተተፍተው እርቃናቸውን ቀርተው፣
መች ይኖሩ ነበር በቁማቸው ሞተው!

ህሊናቸውን ሸጠው፣ ሥጋቸውን ሸጠው..፣
ነፍሳቸውን ሸጠው...
ህይወት-አልባ አካል ሬሳ ታቅፈው፣
አማላጅ በሆኑ ከርሳሞች... ተገዝተው፣
በሆድ ሊደልሉህ ያገር ሃቅን ክደው...፤

«እምቢኝ አሻፈረኝ... ከርቸሌ ይሁን ቤቴ፣
ያሜሪካ ኑሮ... ምኞት ነው ጠላቴ...፣»
ብለህ መለስካቸው? ሃፍረት አሸክመህ?!
ለሕዝብ ልዕልና ለፍትህ ወግነህ!!

እነሱ «እንደኖሩት» መኖር እንዳትሻ
ቆርጠህ ስትነግራቸው፣
ከፊትህ የቆመው በድን አካላቸው፣...
ምናለ ሬሳቸው?!

ትቢት፣ መሃይምነት፣ ጨለማ ጠመንጃ...
ለተጋረጣቸው፣
ክፋት፣ ምቀኝነት፣ በቀል፣ ዘረኝነት...
ለሰረጸባቸው፣
መልካም ትምህርት ልትሰጥ...፣
ቁምነገር ልትሰራ፣
የሻማ ብርሃን ፀዳል ልታበራ፣
ርግብ ሆነህ በረህ፣ አድማስን አቋርጠህ፣
ወይራ ዝንጣፊ፣ ዘምባባ ታቅፈህ፣
ለነጻነት ክብር ልትከፍል ዋጋ፣
ወህኒ ቤት ላለኸው ፍትህን ፍለጋ፡፡

ጌታቸው አበራ
ተጻፈ- (1989 ዓ.ም.)
አምስተርዳም - ሆላንድ

---

***ማስታወሻ፡-***

ይህቺን ግጥም ለአቶ አበራ የማነአብ ማስታወሻ ትሆን ዘንድ የጻፍኳት እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ1989 ዓ.ም. የዛሬ 13 ዓመታት ገደማ ነበር፡፡ አቶ አበራ የማነአብን በግል አላውቃቸውም፡፡ በ1985 ዓ.ም. በፈረንሳይ አገር በፓሪስ ከተማ በተደረገው የኢትዮጵያውያን የሰላምና የዕርቅ ኮንፈረንስ ላይ ተካፋይ የነበሩ ኢትዮጵያውያን በአውሮፓ ከተሞች እየተዘዋወሩ ገለጻ በሚያደርጉበት ወቅት፣ አቶ አበራን በአካል ለማየት አንድ ጊዜ ብቻ ዕድል ገጥሞኝ ነበር፡፡ በዚያው ዓመት ቀጣዩን የሰላምና የዕርቅ ኮንፈረንስ አዲስ አበባ ላይ ለማድረግ ወደ አገር ቤት ከተጓዙት ልዑካን አንዱ ሆነው ሄዱ፤ ለሰላምና ለዕርቅ ያልታደለው ወያኔ ግን፣ አቶ አበራ የማነአብን ቦሌ አየር ማረፊያ ጠብቆ፣ ወደ ሰላሙ አዳራሽ ሳይሆን፣ ወደ ወህኒ ቤት ከተታቸው፡፡ እነሆ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ያለፍርድና ያለፍትህ በወያኔ የግፍ እስር ቤት ውስጥ ሲማቅቁ አስራ ሰባት ዓመታት ተቆጠሩ፡፡

ዛሬ ይህቺን ግጥም ከብዙ ዓመታት በኋላ በድጋሚ ለንባብ ያበቃኋት፣ አበራ የማነአብንና በእሳቸውም ውክልና፣ በዓላማ ጽናታቸውና በአመለካከታቸው ልዩነት ሳቢያ፣ በመላ አገሪቱ በሚገኙ የወያኔ/ኢህአዴግ እስር ቤቶች በግፍ የሚማቅቁ ዜጎቻችንን ሁሉ ለማሰብ ነው፡፡

በአዲሱ ዓመት ለህሊናና ለፖለቲካ እስረኞች በሙሉ፣ ቸሩ እግዚአብሔር ፍትህን አጎናጽፏቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተቀላቅለው በፍቅር ሊኖሩ ይችሉ ዘንድ ጽኑ ምኞቴ ነው! አሜን!

ጌታቸው አበራ
መስከረም 2003 ዓ/ም
(ሰፕቴምበር 2010)